# ወይ አንተ !

# የግንቦት 7 ባንዳ ሽቃቦችና የኢሳያስ ጫማ ላሾች ነፃ ያወጡኛል ብለህ የምታስብ ከሆነ፣ አእምሮህ በጋራጋንቲ ተሞልቶ ልብህ ውስጥ ግዙፍ እብደት አለ ማለት ነው።

ከአስተዋይ በቀለ

እንደ ሰዱቃውያን በአደባባይ ጡሩምባህን በግብዝነት ስትነፋና እንደ ወያኔ አቡጀዲ በባዶ ቤት ስትቀደድ እስከ ዛሬ ያልተገታ መከራና ግፍ በአገራችንና በሕዝባችን ላይ እየተቀለለ ነው።

ወይ ቀርጣፊ ጥርስ ወይ አኛኪ መንጋጋ ሳይኖርህ እንዲያው በድድህ ተቃዋሚ ፖለቲከኛ ነኝ ብለህ እንደ ግብዝ ፈሪሳውያን ስትመፃደቅ ይኸው ዓመታት አለፉ።

እንኳን የሜዳ አህዮችን ልታባርርና አገር ልታድን ቀርቶ፣ ጠንካራና የላቀ ድርጅት መፍጠር፣ ብልህነትና ማስተዋል የተሞላ፣አያያዝና ቆራጥ አካሄድ ጠፍቶብህ የተሳፈርህበት የተቃውሞ ባቡር እዚያው ሽመንደፈር እንደቆመ ነው።ተቃውሞህም ከመቆርቆርና ከፊን _ ፊን እንቅስቃሴ ባሻገር ጠፍ ባድማ ሆኗል።

ለመሆኑ ምንም ጠብ ላይል እዚያው ብዙ ጊዜ ቁጭ ብሎ ማማጥ ትርፉ መቀመጫ የሚያሳጣ ኪንታሮት እንደሆነ  ሐኪሞች አልነገሩህም እንዴ ? ወይስ ሀሳብህ ሌላ ነው ?

አንተ እኮ አድርባይነትና ቅሌቱ አያጣህም።ግንቦት 7ና የሻቢያ ጦር ነፃ ያወጣኛል ብለህ አስበህ ከሆነ፣ልብህ ውስጥ ግዙፍ እብደት አለ ማለት ነው።

ወዮልህ ! ግንቦት 7 ኤርፎርስ አንድ መስሎህ አብረህ ለመሳፈር ጭራህን ከቆላህና አብረህ የኢሳያስን ጫማ እየላስህ በኢትዮጵያ፣ በኢትዮጵያዊነትና በሰንደቅ ዓላማችን ላይ አብረህ ጉድጓድ ከማስህ አንተው ራስህ አብረህ ትገባባታለህ።

የምትሰማ ከሆነ በግንቦት 7ና በኢሳያስ ላይ መተማመኑን ተው።ይልቅስ የሕይወት መስዋዕትነት ለመክፈል የቆረጡና በትግል ቃለ _ መሃላ የተሳሰሩ ግለሰቦችን ያቀፈ የፖለቲካ ድርጅት፣ ብቃትና ሕዝባዊ ድጋፍ በአስቸኳይ ፍጠርና ወራሪ የሜዳ አህዮችን አጥፍተህ አገርህን አድን።አይዞህ መንገድህ ጨርቅ ነው። ደጋፊህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ።በርታ !